## የMCPS የምረቃ መጠን እያደገ ነው

ጃንዩ. 28 በMaryland State Department of Education (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ) (MSDE) በሰጠው መግለጫ የMontgomery County Public Schools (MCPS) የአራት አመት የምረቃ መጠን ወደ 88.3 በመቶ አድጓል። ከ =2012 ተመራቂዎች ጋር ሲመዛዘን የMCPS ምረቃ መጠን በአንድ በመቶ አቅራቢያ ያደገ ሲሆን ባለፉት ሁለት አመታት በ1.5 በመቶ ነጥቦች አድጓል።

የ2013 ተመራቂዎች የMCPS የምረቃ መጠን ከሜሪላንድ ስቴት መጠን በ3.3 መቶኛ ነጥቦች ልቆ ይገኛል።

Superintendent of Schools Joshua P. Starr እንዳለው፣ "የምረቃ መጠናችን ዘላቂ እድገት ለተማሪዎቻችንና ለሰራተኞቻችን ብርቱ ስራ፣ እና ለወላጆቻችና ለህብረተሰብ አባሎቻችን ድጋፍ አንድ ምስክር ነው። ሁሉም ተማሪዎች ለወደፊታቸው ከሚያስፈልጓቸው ሙያዎችና እውቀት ጋር መመረቃቸውን ለማረጋገጥ ግዴታ ገብተናል።"

በተጨማሪም ለ1013 ተመራቂዎች አቋርጠው የሚሄዱትንም ቁጥር መጠን MSDE መግለጫ ሰጥቷል። ለMCPS፣ አቋርጦ የመውጣቱ መጠን ወደ 6.3 በመቶ ወርዷል — ይህም የአንድ-አመት 0.5 በመቶ ቅናሽ እና የሁለት-አመት 1.1 በመቶ ቅናሽ። የMCPS አቋርጦ የመውጣት መጠን ከስቴቱ የ9.4 በመቶ መጠን በ3.1 በመቶ ነጥብ ያንሳል።

[በተጨማሪ ይማሩ]

## ሶስት የMCPS ተማሪዎች የኢንቴል ሳይንስ የመጨረሻ ማጣርያ ተወዳዳሪ ተብለው ተሰየሙ።

ከMontgomery Blair 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ሶስት በማቆጥቆጥ ላይ የሚገኙ የMCPS ሳይንቲስቶች፣ በሃገሪቱ ውስጥ እጅጉን ክብር ከሚያስገኙ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሳይንስ ውድድሮች አንዱ የሆነው፣ የ2014 ኢንቴል ሳይንስ የባለ ተሰጥኦ ፍለጋ የማጣርያ እጩዎች ሆነው ተመርጠዋል።

Montgomery Blair 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በህገሪቱ ውስጥ ከሚገኝ ማንኛውም ት/ቤት እጅጉን የላቁ የማጣርያ ተወዳዳሪዎች አሉት። ሶስቱ የማጣርያ ተወዳዳሪዎች እና ፕሮጀክቶቻቸው እነዚህ ናቸው፦

- Ishaun S. Datta (ኢሻውን ኤስ. ዳታ)፣ *Saturated Nuclear Matter in the Large Nc and Heavy Quark Limits of Quantum Chromodynamics (የኑክሌያር-ነክ ንጥረነገሮች ምርምር)*
- Neil S. Davey (ኒይል ኤስ ዴቪይ)፣ *Early Cancer Diagnosis and Treatment Through the Detection of Circulating Tumor Cells Using Drop-Based Microfluidics (የካንሰር-ነክ ምርምር)*
- Jessica Shi (ጄሲካ ሺ)፣ *The Speeds of Families of Intersection Graphs*

ኢንቴል ሳይንስ የባለተሰጥኦ ፍለጋን የሚያስተዳደረው በሳይንስና ትምህርት ህዝባዊ ተሳትፎን የማበረታታት አላማው ባደረገው በSociety for Science & the Public (የሳይንስና የህዝብ ማህበር) ተብሎ በሚጠራው የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው። የማጠቃለያው ተወዳዳሪዎች የ$100,000 ታላቅ ሽልማትን በሚያጠቃልለው ከ$600,000 በላይ ለተዘጋጁ ሽልማቶች ለመወዳደር ከማርች 6 እስከ 12 ድረስ ዋሺንግተን፣ ዲሲ፣ ይሰባሰባሉ።

ባለፈው ወር፣ የሳይንስና የህዝብ ማህበር (Society for Science & the Public)፣ 1,800 ከሚደርሱ የተወዳዳሪዎች ክምችት የተመረጡ፣ የ300 የግማሽ ፍፃሜ ተወዳዳሪዎች ስም አስታውቋል። ከሜሪላንድ 20 የግማሽ ፍፃሜ ተወዳዳሪዎች 75 በመቶ የሆኑት አስራአምስት የMCPS ተማሪዎች የግማሽ ፍፃሜ ተወዳዳሪዎች ሆነው ተመርጠዋል። ከአራቱ የሜሪላንድ የግማሽ ፍፃሜ ተወዳዳሪዎች MCPS ሶስቱን ይዟል።

ስለ የፍፃሜ ተወዳዳሪዎችና ስለፕሮጀክቶቻቸው ይበልጥ ለማወቅ ይህን ቪዲዮ ተመልከቱ።

## አስራዘጠኝ የMCPS ተማሪዎች የተሟላ የፖሴ (Posse) ስኮላርሺፕ ተቀበሉ

አስራዘጠኝ የMontgomery County Public Schools (MCPS) ተማሪዎች ከPosse Foundation (የፖሴ በጎአድራጎት ድርጅት) የተሟላ የአራት አመት ሙሉ የኮሌጅ ስኮላርሺፕ ተቀባዮች ተብለው ተሰይመዋል።

የPosse ፕሮግራም በዘልምድ የኮሌጅ ምርጫ ሂደት ተዘለው ሊሆኑ የሚችሉ ልዩ አካዴሚያዊና የአመራር እመርታ ያላቸው የ2ኛ ደረጃ ህዝባዊ ት/ቤት ተማሪዎችን ይለያል። አርባአራት ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች እያንዳንዳቸው ሁለገብ/የተሟላ ስኮላርሺፕ በአገር-አቀፍ ደረጃ ለተማሪዎች በመስጠት በያንዳንዱ ካምፐስ ፖሴዎች (Posses) የሚባሉ ባለበርካታ ባህል ቡድኖች በመፍጠር ላይ ይገኛሉ። እነዚህ የተማሪ ቡድኖች የባለሙያ አመራር በቅድሚያና ኮሌጅ ባሉበት ወቅት በሙሉ ያገኛሉ እርስ በርሳቸውም ይደጋገፋሉ። በካምፐስ ውስጥ፣ እነዚህ ተማሪዎች በአስፈላጊ የአመራር ሚና ያገለግላሉ።

የPosse ፕሮግራሞች በተለያዩ ዘጠኝ አካባቢዎች ይገኛሉ — አትላንታ፣ ቦስቶን፣ ቺካጎ፣ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ፣ ሂውስተን፣ ሎሰንጄለስ፣ ሚያሚ፣ ኒው ኦርሊንስ እና ኒው ዮርክ — እናም 1,600 የሚደርሱ ተማሪዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ለስኮላርሺፖች ይሰየማሉ።

የዚህ አመት የMCPS ተቀባዮች ከ11 የተለያዩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመጡ ሲሆን ስድስት የተለያዩ ኮሌጆች ይከታተላሉ።

[የተቀባዮቹን ስም ዝርዝር ተመልከቱ]

## የሰመር እድሎች በአል (Summer Opportunities Fair) ለፌብሩ. 27 ተመደበ

ወላጆች ለት/ቤት የደረሱ ልጆች በርካታ የሰመር እድሎች ሀሙስ፣ ፌብሩ. 27 በሚከበር በአል መዳሰስ ይችላሉ። የቅርብና የሩቅ አካባቢ አቅራቢዎች ስለ ሰመር ካምፖች፣ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች ለመነጋገር ይገኛሉ። በበአሉ ወቅት ፣ የፕሮግራም ሰራተኞችን ይገናኛሉ ፣ ማመልከቻዎችን ይወስዳሉ ፣ እና ስለፋይናንሳዊ እርዳታ መረጃ

ማግኘት ይችላሉ። በአሉ ከ7 እስከ 8:30 p.m በRichard Montgomery High School, 250 Richard Montgomery Drive in Rockville ይከናወናል።

የስፕሪንግ ፕሮግራሞች በMontgomery County የመዝናኛ መምርያ ይቀርባል ምዝገባ የሚጀምረውም ሰኞ፣ ፌብሩ. 10 ነው። ፕሮግራሞቹ አመች በሆኑ ቦታዎች በመላ ካውንቲው ይቀርባሉ። ወላጆች ከአራት አማራጮች በአንዱ መመዝገብ ይችላሉ፡- በፖስታ፣ በፋክስ፣ [በመስመር ላይ]፣ ወይም በግል 4010 Randolph Road፣ Silver Spring በሚገኘው የመዝናኛ መምርያ በመገኘት ስለ ስፕሪንግ ፕሮግራሞች መግለጫ/መመርያ በሁሉም የመዝናኛና የውሀ ማእከሎች (aquatic centers) ወይም መስመር ላይ (online) ይገኛል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ 240-777-6840 ይደውሉ።

**የ2ኛ ደረጃ የኮርስ መፅሄት (High School Course Bulletin) መስመር ላይ ይገኛል**

የ2014-2015 [የ2ኛ ደረጃ የኮርስ መፅሄት (High School Course Bulletin)] አሁን መስመር ላይ ይገኛል እናም በMCPS 2ኛ በረጃ ት/ቤቶች የሚሰጡ የተለያዩ ኮርሶች ዝርዝር ያቀርባል። የመመርያ አማካሪዎች (Guidance counselors) የመፅጄቱን ቅጅዎች ለስምንተኛና ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ያድላሉ።

[High School Course Bulletin (የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት የኮርስ መፅሄት)]

**የHBCU በአል ለፌብሩ. 19 ተመድቧል**

Historically Black College and Universities (ታሪካዊ ጥቁር ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲዎች) (HBCU) Fair (በአል) **ሮብ፣ ፌብሩ. 19** ከ6 እስከ 8 p.m በRichard Montgomery 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ 250 Richard Montgomery Drive in Rockville ይከበራል (የበረዶ ቀን፡- ፌብሩ. 20)። ሁሉም የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችና ወላጆቻቸው እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። ከ60 በላይ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ስለ ፕሮግራሞቻቸው ከወላጆችና ከተማሪዎች ጋር ለመነጋገር በበአሉ ላይ ይገኛሉ። በርካታ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች

QuickNotes mcps

ለመመዝገብ ለሚፈልጉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ቦታው ላይ ቃለመጠይቅ ያደርጋሉ። የተሳታፊ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ዝርዝር እንዲሁም ማምጣት የሚያስፈልጉ ሰነዶች ጥቆማን ጨምሮ፣ ስለ በአሉ ተጨማሪ መረጃዎች እዚህ ይገኛል።

የHBCU በአል

## የኮንሶርሺያና የማግኔት ማመልከቻ ዜናዎች

ፌብሩዋሪ መባቻ ላይ፣ የNortheast Consortium (NEC) እና የDowncounty Consortium (DCC) ኮንሶርሺያዎች የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ወላጆች ለ2014-2015 የትምህርት ዘመን የ2ኛ ደረጃ ምደባ ደብዳቤ በፖስታ ይደርሳቸዋል። ደብዳቤው ስለመጪ የምዝገባ ስብሰባዎች ዝርዝሮች ይይዛሉ። የምዝገባ ስብሰባ ለአምስቱም የDCC 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ እና ለBlakeና ለSpringbrook 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች **ሮብ፣ ፌብሩ. 5 በ7 p.m. ይከናወናል።** ለPaint Branch 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የምዝገባ ስብሰባ የተመደበው **ለሀሙስ፣ ፌብሩ. 6 ነው።** (Snow date (የበረዶ ቀን) ለሁሉም 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች:- ፌብሩ. 11)

በተጨማሪ፣ ለMiddle School Magnet Consortium (MSMC) ያመለከቱ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ወላጆች የማስታወቂያ ደብዳቤ በፖስታ ይደርሳቸዋል። ለ2ኛ ደረጃ ማግኔት ፕሮግራሞች ያመለከቱ የአምስተኛና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ወላጆችም የማሳሰብያ ደብዳቤ በዚሁ ወር ይደርሳቸዋል (የ2ኛ ደረጃ ማግኔት ፕሮግራሞች የሚያካትቷቸው Roberto Clemente፣ Eastern እና Takoma Park መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና Montgomery Blair፣ Poolesville እና Richard Montgomery 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ነው)።

የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ምርጫ ፎርሞች ለNEC እና DCC አዳዲስ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች እና የNEC እና የDCC መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች በዝውውር 8ኛ ክፍል የሚከታተሉ ተማሪዎች በፖስታ ይላክላቸዋል።

በMSMC አዲስ ነዋሪዎች ለሆኑ ለ5ኛ ክፍል ተማሪዎች በፖስታ የሚላኩትን ሁለተኛ ዙር የምርጫ ፎርሞችን ወላጆች መጠባበቅም አለባቸው። የ5ኛ ክፍል ተማሪ ወላጆች በMontgomery County ሌሎች አካባቢዎች የሚኖሩ እና ለ2014-2015 የትምህርት ዘመን

በMSMC ት/ቤቶች ለማመልከት ፍላጎት ያላቸው፣ የምርጫ ፎርሞ ከ[MCPS ድር ጣብያ] ሊገኝ ይችላል።

*የምርጫ ለውጥ ፎርሞች (Change of Choice Request Forms)* በ 21014-2015 የትምህርት ዘመን የኮንሶርሺያ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት መለወጥ ፍላጎት ያላቸው አሁን ከ9 እስከ 11 ያሉ ተማሪዎች በNEC እና በDCC 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የምክር ፅ/ቤቶች (counseling offices) ማግኘት ይችላሉ።

*አሁን በ6ኛ ክፍል የሚገኙና የMSMC ት/ቤት ለውጥ መጠየቅ ለሚፈልጉ የMSMC ተማሪ ወላጆች የምርጫ ለውጥ ፎርሞች* በMSMC የመካከለኛ ደረጃ የምክር ፅ/ቤቶች (counseling offices) ማግኘት ይችላሉ።

በ2ኛ ዙር ምርጫ እና *የምርጫ ለውጥ* ሂደት የመሳተፊያ የጊዜ ገደብ አርብ፣ ፌብሩ. 14 ነው። የማሳሰቢያ ደብዳቤዎች ወደ ተማሪዎች ቤቶች በማርች አጋማሽ በፖስታ ይላካሉ።

[የኮንሶርሺያ ምርጫና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎት (Consortia Choice and Application Program Service)]

**ለኤሌሜንታሪ ኢመርሽን ፕሮግራም ማመልከቻዎች አሁን ይገኛሉ**

የኤሌሜንታሪ ት/ቤት የቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራሞች የሚጀመሩት በሙአለህፃናት ሲሆን የሚቀርቡትም በቻይኒዝ፣ ፈረንሳይኛና ስፓኒሽ ነው። በ2014-2015 የትምህርት ዘመን ከሙአለህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል ለሚገቡ ተማሪዎች ማመልከቻዎች አሁን ይገኛሉ። ስለ ኤሌሜንታሪ ኢመርሽን ፕሮግራሞች ተጨማሪ መርጃዎች እና *የኢመርሽን ፍላጎት ፎርም (Immersion Interest Form)*፣ [ለማውረድ (to download) የልዩ ፕሮግራሞች (Special Programs) ድር ጣብያ] ይጎብኙ። እንዲሁም ፎርሞቹ አሁን በኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች ይገኛሉ። የ2014-2015 የትምህርት ዘመን የማመልከቻ ገደብ አርብ፣ ኤፕሪል 4 ነው። በግንቦት ወር የማስታወቂያ ደብዳቤዎች ለወላጆች በፖስታ ይላካሉ።

**አትርሱ**

**የትምህርት ቦርድ ለ17ኛው አመታዊ ሽልማቶች ለህዝባዊ ትምህርት የላቀ አገልግሎት** (Distinguished Service to Public Education) **የእጭዎች ስያሜ ከህዝብ እየፈለገ ነው። ቦርዱ ሽልማቶቹን ያቋቋመው ለህዝባዊ ትምህርትና ለ**MCPS **የላቀ አስተዋፅኦዎች ላደረጉ እውቅና ለመስጠትና አድናቆት ለማሳየት ነው።**

**የመሰየሚያ ፎርሞች በ[ትምህርት ቦርድ ድርጣብያ] ማግኘት ይቻላል። የተሞሉ ፎርሞች ገቢ መሆን ያለባቸው** በ5 p.m. **ማክሰኞ፣ ፌብሩ. 11 ነው።**

**ያስታውሱ ...**

**ክብርን ይምረጥ ስብሰባ** (Choose Respect Conference) **እሁድ፣ ፌብሩ. 23 ይካሄዳል።** ስብሰባው በMontgomery College **ባህላዊ ኪነት ማእከል፣ ታኮማ ፓርክ** ከ1 እስከ 4:30 p.m.፣ **ይከናወናል።**
**ክውነቱ ነፃ ነው እናም** ከ8ኛ እስከ 12ኛ **ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች ክፍት ነው። ተሳታፊዎች በእርስበርስ ግንኙነት፣ የትምህርት ዎርክሾፖች የመሳተፍ እድል ይኖራቸዋል። እጣዎች፣ ሽልማቶች፣ ነፃ ምግብ እና፣** በEclipse Performing Dance Company **ትርእይት የሚያካትት፣ ልዩ እውን መዝናኛዎችም ይኖራሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣** 240-777-7075 **ደውሉ።**

[ምዝገባ]

**እንዲሁም...**

**ስለ ኮሌጅ እና እንዴት እንደሚከፍሉበት ማሰብ/መጨነቅ ከጀመሩ፣ እሁድ፣ ፌብሩ. 9 እና ሀሙስ፣ ፌብሩ. 27** በMontgomery College **በሚከናወኑ የ**2014 **የኮሌጅ ግብ** እሁድ (College Goal Sunday) **ክውነቶች ተገኝተው ይማሩ። የ**College Goal Sunday **ቀኖችና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-**

**ፌብሩ. 9፣ 2-4 p.m.** (የበረዶ ቀን፣ - ፈብሩ. 16)
Montgomery **ኮሌጅ ታኮማ ፓርክ/ሲልቨር ስፕሪንግ ካምፐስ**
7625 Fenton Street, Takoma Park, Charlene R. Nunley Student Services Center

**ፌብሩ. 27፣ 4-6 p.m.** (የበረዶ ቀን፡ - ማርች 6)
Montgomery **ኮሌጅ ጀርማንታውን ካምፐስ**
20200 Observation Drive, Germantown, High Technology and Science Center (HT Building)

**ለተጨማሪ መረጃዎች** College Goal Maryland **ድር ጣባያ ይጎብኙ።**